የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች በገቢ ማስገኛ ሥራዎች ላይ የሚሰማሩበትን ሁኔታ ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር 937/2015

Directive to Determine the Conditions Under Which Civil Society Organizations Are Engaged in Income-Generating Activities (Directive No. 937/2022)

የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የሲቪል ሰርቪስ ድርጅቶች ባለስልጣን
F.D.R.E Authority for Civil Society Organizations

ታኅሣሥ 13፥ 2015

ስለ ድርጅቶች መዋሃድ፣ መከፋፈል፣ መለወጥና መፍረስ የወጣ መመሪያ

መመሪያ ቁጥር 936/2015"

በሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር 1113/2011 አንቀጽ 80 መሠረት ቁጥራቸው ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ድርጅቶች አግባብነት ባላቸው ሕጎችና በመተዳደሪያ ደንባቸው መሠረት በአዲስ ስም ወይም ከሚዋሐዱት ድርጅቶች በአንዱ ስም ሊዋሐዱ እንደሚችሉ የተደነገገ በመሆኑ፤

በተጠቀሰው አዋጅ አንቀጽ 81 እና 82 አንድ ድርጅት በመተዳደሪያ ደንቡ ላይ በተመለከተው መሠረት በድርጅቱ የበላይ አካል ውሳኔ ሊከፋፈል ወይም ወደ ሌላ ዓይነት ድርጅት ሊለወጥ እንደሚችል የተደነገገ በመሆኑ፤

በአዋጁ አንቀጽ 83 እና 84 መሰረት ድርጅቶች ሊፈረሱ የሚችሉባቸው መንገዶች እና ውጤቱ የተገለጸ በመሆኑ፤

ከላይ የተጠቀሱትን ድንጋጌዎች ለማስፈጸም መመሪያ ማውጣት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ባለስልጣን በአዋጁ አንቀጽ 89 ንዑስ አንቀጽ (2) በተሰጠው ሥልጣን

DIRECTIVE ON MERGERS, DIVISIONS, CONVERSIONS AND DISSOLUTIONS OF ORGANIZATIONS

DIRECTIVE NO 936/2022

WHEREAS, according to Article 80 of Civil Society Organizations Proclamation No. 1113/2019, two or more organizations may merge under a new name or the name of one of the merged organizations in accordance with relevant laws and regulations;

WHEREAS, it is stipulated in Articles 81 and 82 of the aforementioned proclamation that an organization may be divided or transformed into another type of organization by the decision of the superior body of the organization as per the regulations;

WHEREAS, according to Article 83 and 84 of the Proclamation, the means by which organizations can be dissolved and the consequences are stated;

NOW THEREFORE, as it is necessary to issue a directive to implement the above provisions, the Authority of Civil Society Organizations has issued this directive as per the powers vested in it by Article 89(2) of

መሠረት ይህን መመሪያ አውጥቷል፡፡

ክፍል አንድ
ጠቅላላ

1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "ስለ ድርጅቶች መዋሃድ፣ መከፋፈል፣ መለወጥና መፍረስ የወጣ መመሪያ ቁጥር 936/2015" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር፣ በዚህ መመሪያ ውስጥ፤

1) "አዋጅ" ማለት የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር 1113/2011 ነው፤

2) "ድርጅት" ማለት በአዋጁ አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ (1) ትርጓሜ የተሰጠው የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅት ነው፤

3) "ባለስልጣን" ማለት በአዋጁ አንቀጽ 4 መሰረት የተቋቋመው እና የፌዴራል መንግስት አስፈጻሚ አካላትን ስልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 1263/2014 (እንደተሻሻለ) የስያሜ ለውጥ በማድረግ የተቋቋመው "የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ባለስልጣን" ነው፡፡

the Proclamation.

PART ONE

GENERAL

1. Short title

This Directive may be cited as "Directive No 936/2022 on the Merger, Division, Conversion and Dissolution of Organizations".

2. Definitions

Unless the context requires otherwise, in this directive:

(1) "Proclamation" means Civil Society Organizations Proclamation No. 1113/2011;

(2) "Organization" means a civil society organization as defined in Article 2(1) of the Proclamation;

(3) "Authority" means "Authority of Civil Society Organizations" which was established in accordance with Article 4 of the Proclamation and which was established by Decree No. 1263/2014 (as amended) to determine the powers and functions of the executive bodies of the Federal Government by changing its name.

4) "ሰው" ማለት ማናቸውም የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤
5) በአዋጁ የተሰጡ ትርጓሜዎች ለዚህ መመሪያም ተፈፃሚ ይሆናሉ፤
6) በወንድ ፆታ የተገለጸው አነጋገር የሴት ፆታንም ይጨምራል፡፡

3. የተፈጻሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ በማንኛውም ድርጅት ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

ክፍል ሁለት
ስለ ውህደት፣ መከፋፈል እና መለወጥ

4. መሠረቱ

የድርጅቶች ውህደት፣ መከፋፈልና መለወጥ አላማ ለኅብረተሰቡ የተሻለ ጥቅም ለማስገኘት በተለይም የተጠቃሚዎችን ጥቅም ለማስጠበቅ መሆኑን ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡

5. ስለውህደት

1) ማንኛውም ድርጅት በአዋጁ አንቀጽ 80 በተደነገገው መሠረት በመተዳደሪያ ደንቡ ወይም አግባብ ባለው ሕግ መሠረት ከአንድ ወይም ከዚያ በላይ ከሆኑ ድርጅቶች ጋር በድርጅታቸው የበላይ አካላት ውሣኔ የውህደት ስምምነት በመፈጸም በአዲስ ስም ወይም ከሚዋሐዱት ድርጅቶች በአንዱ ስም ሊዋሐድ ይችላል፡፡

(4) "Person" means any natural person or legal entity;
(5) Definitions given in the proclamation shall also apply to this directive;
(6) Expressions in the male gender includes the female gender.

3. Scope of application

This directive applies to any organization.

PART TWO
MERGER, DIVISION AND TRANSFORMATION

4. Purpose

It is necessary to ensure that the purpose of the merger, division and transformation of organizations is to achieve better benefits for the society, especially to protect the interests of the users.

5. Merger

(1) Any organization may merge with one or more organizations under a new name or under the name of one of the merging organizations by making a merger agreement with one or more organizations in accordance with the provisions of Article 80 of the Proclamation.

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት በሀገር ውስጥ ተመዝገቦ በመንቀሳቀስ ላይ ባለ የውጭ ድርጅት እና በሀገር በቀል ድርጅት መካከል የሚደረግ መዋሃድ፤

(ሀ) ውህደቱ የውጭ ድርጅቱን ወደ ሀገር በቀል ድርጅትነት ለመለወጥ ከሆነ በሚዋሀደው አገር በቀል ድርጅት ውስጥ በመጠቃለል ወይም በአዋጁ ከተመለከቱት አገር በቀል ድርጅቶች ዓይነት በአንዱ በአዲስ ስም በመዋሃድ፤

(ለ) ከንብረት ጋር በተያያዘ በውጭ ሀገር ደርጅት ላይ ተፈጻሚ የሚሆኑ ሕጎች እንደተጠበቁ ሆነው፣ ውህደቱ ሀገር በቀል ድርጅትን ወደ ውጭ ድርጅትነት የሚለወጥ የሆነ እንደሆነ ሀገር በቀል ድርጅቱ ውጭ ሀገር በተቋቋመው የውጭ ድርጅት ሥር በመጠቃለል ሊፈጸም ይችላል፡፡

3) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) (ሀ) በሚፈጸም ውህደት ላይ አገር በቀል ድርጅትን የሚመለከቱት የአዋጁ ድንጋጌዎች ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡

4) በመተዳደሪያ ደንባቸው መሠረት ውሕደቱ ሲፈጸም የቀድሞዎቹ ድርጅቶች መብትና ግዴታዎች እንዲሁም በውስጣቸው የነበሩ ሰራተኞች እንደአግባብነታቸው በውህደት ወደተፈጠረው ድርጅት ይተላለፋሉ፡፡

(2) A merger between a foreign company registered and operating in the country and a local company in accordance with paragraph 1 of this article shall be done as follows:

a) If the merger is to convert the foreign company into a local company, by merging with the local company being merged or merging with a new name of one of the types of local companies specified in the decree;

b) Subject to the laws applicable to foreign companies in relation to assets, if the merger is to transform a domestic company into a foreign company, the domestic company may be consolidated under a foreign company established abroad.

(3) Paragraph (2) (a) of this Article shall apply the provisions of the Proclamation relating to indigenous organizations to mergers.

(4) When the merger takes place in accordance with their bylaws, the rights and obligations of the previous organizations as well as the employees in them shall be transferred to the merged organization.

5) በሚዋሀዱ ድርጅቶች መካከል አስቀድሞ የተደረገ ተቃራኒ ስምምነት ከሌለ በስተቀር ውህደቱ ከተፈጸመ በኂላ ቀድሞ እያንዳንዱ ድርጅት ላይ ያሉ እዳዎች ሙሉ በሙሉ ወደ ተዋሀደው ድርጅት ይተላለፋሉ፡፡ ሆኖም ግን በዚህ ንኡስ አንቀጽ መሰረት በሚዋሀዱ ድርጅቶች መካከል እዳን በተመለከተ አስቀድሞ የሚደረግ ስምምነት የአበዳሪዎችን መብት በሚጎዳ መልኩ መሆን የለበትም፡፡

6. **በውህደት ስለተፈጠረ አዲስ ድርጅት ምዝገባ**

1) በውሕደቱ የተፈጠረው አዲስ ድርጅት በአዋጁ በተደነገገው መሠረት በባለስልጣኑ መመዝገብ አለበት፡፡

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ድርጅትን ለማስመዝገብ ከሚቀረብ የምዝገባ ማመልከቻ ጋር የሚከተሉት ሰነዶች ተያይዘው መቅረብ ይኖርባቸዋል፤

(ሀ) ውህደቱ እንዲፈጸም በመተዳደሪያ ደንቡ ሥልጣን በተሰጠው የበላይ አካል የተላለፈውን የእያንዳንዱን ድርጅት ውሳኔ፤

(ለ) ውህደቱን የሚፈጽሙት ድርጅቶች ተወካዮች ውህደቱ እንዲፈጸም ያደረጉትን ስምምነት፤

(ሐ) ውህደት ከመፈጸሙ በፊት የነበረውን የእያንዳንዱን ድርጅት መተዳደሪያ

(5) Unless there is a prior agreement to the contrary between the merging companies, after the merger, the liabilities of each company shall be fully transferred to the merged company. Provided, however, that any prior agreement regarding debts between companies merging under this paragraph shall not prejudice the rights of creditors.

6. Registration of a new company created by merger

(1) The new company created by the merger shall be registered by the authority in accordance with the provisions of the Proclamation.

(2) According to paragraph 1 of this article, the following documents shall be submitted with the registration application to register an organization:

a) The resolution of each organization passed by the governing body empowered by the bylaws to carry out the merger;

b) The consent of the representatives of the merging companies to effect the merger;

c) The articles of association and

ደንብ እና የምዝገባ ሰርትፍኬት፤

(መ) የተዋሃደውን የእያንዳንዱን ድርጅት የሀብትና ዕዳ መግለጫዎች እና የንብረት ቆጠራ ዝርዝር፤

(ሠ) ከውህደቱ በፊት የነበረውን የእያንዳንዱን ድርጅት ሠራተኞች ስም ዝርዝርና የከፈሉትን የግብርና የጡረታ መዋጮ የሚያሳይ መግለጫ እንዲሁም ወደ ተዋሃደው ድርጅት የተላለፉትን ሠራተኞች ስም ዝርዝር ፤

(ረ) **የተዋሃደውን የእያዳንዱን ድርጅት ወቅታዊ የኦዲት ሪፖርት፤**

(ሰ) **የተዋሃደውን የእያዳንዱን ድርጅት ገንዘብ ጠያቂዎች ስም ዝርዝር እና ውህደቱን በተመለከተ ገንዘብ ጠያቂዎች ያደረጉትን ስምምነት፤**

(ሸ) የሚዋሀደውን ድርጅት መተዳደሪያ ደንብ እና የድርጅቱን የስራ መሪዎች ስም፣ አድራሻ እና ዜግነት፤

(ቀ) እያንዳንዱ ድርጅት ከመዋሃዱ በፊት በስሙ ተከፍቶ ስለነበረው የባንክ ሂሣብ መግለጫ

(በ) ድርጅቶቹ በአዲስ ስም ውህደት ከፈጸሙ የደርጅቱን ስምና ዓርማ (ካለው)፤

(ተ) የተዋሃደው ድርጅት የሚሰማራበትን የሥራ ዘርፍ፤

(ቸ) የተዋሃደው ድርጅት አድራሻ፡፡

certificate of incorporation of each organization prior to the merger;

d) A statement of assets and liabilities and an inventory of assets of each amalgamated entity;

e) A list of the employees of each company before the merger and a statement showing taxes and pension contributions they have paid, and a list of the names of the employees transferred to the merged company;

f) The current audit report of each consolidated company;

g) A list of the creditors of each of the merged organizations and the agreements entered into by the creditors in connection with the merger;

h) The articles of association of the merging organization and the names, addresses and nationalities of the organization's officers;

i) Statement of the bank account opened in the name of each company before the merger

j) If the companies have merged with New Wax, the company's name and logo (if any);

k) The field of business in which the merged entity is engaged;

l) Address of the merged organization.

7. በነባር ድርጅት ስም ስለተደረገ ውህደት

በነባር ድርጅት ስም የተደረገ ውህደትን በተመለከተ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ (2) ሥር የተመለከቱት ሰነዶች ውህደቱ ከመፈጸሙ በፊት ለባለስልጣኑ መቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡

8. ስለመከፋፈል

1) ማንኛውም ድርጅት በድርጅቱ መተዳደሪያ ደንብ መሠረት ወይም በድርጅቱ የበላይ አካል ውሳኔ በሁለት ወይም ከሁለት በላይ በሆኑ ድርጅቶች ሊከፋፈል ይችላል፡፡

2) በመከፋፈሉ ውሳኔ ላይ በሌላ ሁኔታ ካልተመለከተ በስተቀር፣ በክፍፍሉ የተፈጠረው እያንዳንዱ ድርጅት የቀድሞው ድርጅት ላለበት ግዴታና መብት እኩል ተካፋይ ይሆናል፡፡

3) የቀድሞው ድርጅት ህልውና የሚያበቃው ለአዲሶቹ ድርጅቶች በባለስልጣኑ የምዝገባ ምስክር ወረቀት ሲሰጥ ነው፡፡

4) በአዲሶቹ ድርጅቶች ሙሉ ስምምነት አንደኛው የቀድሞውን ድርጅት ስም ይዞ ሊቀጥል ይችላል፡፡

5) የበሰለ ወይም ተከፋይ ዕዳ ያለበት የሲቪል ማኅረሰብ ድርጅት ድርጅቱ ከመከፋፈሉ በፊት

7. Merger done on behalf of an existing organization

In the case of a merger on behalf of an existing company, the documents mentioned under paragraph 2 of Article 6 of this directive must be submitted to the authority before the merger takes place.

8. Division

(1) Any organization may be divided into two or more organizations according to the organization's articles of association or by the decision of the organization's governing body.

(2) Unless otherwise specified in the division decision, each company created by the division shall be an equal participant in the obligations and rights of the previous company.

(3) The existence of the former organization ends when the new organizations are issued with a certificate of registration by the authority.

(4) With the full agreement of the new organizations, one of them may continue with the name of the previous organization.

(5) A civil society organization that has matured or payable debts must obtain the consent of the financiers or

የባለገንዘቦችን ወይም የአበዳሪዎችን እና የዋስትና ሰጪዎችን ፈቃድ ማግኘት ይኖርበታል፡፡

6) ለባለገንዘቦች ወይም ለአበዳሪዎች ግዴታ ኖሮበት ለመከፋፈል የታሰበ ድርጅት ግዴታውን መወጣት የማይችል የሆነ እንደሆነ የአበዳሪዎችን ፈቃድ ሳያገኝ ድርጅቱን የመከፋፈል ውሳኔ ሊተላለፍ አይችልም፡፡

7) ሂሣብ እስከሚዘጋበት እና ከመጨረሻው የሂሣብ ዓመት መጀመሪያ አንስቶ መከፋፈሉ እስከሚፈጸምበት ድረስ ያለው የሚከፋፈለው ድርጅት ሂሣብ መመርመር ይኖርበታል፡፡

9. <u>ስለተከፈለ ድርጅት ምዝገባ</u>

1) በክፍፍል የተፈጠረ እያንዳንዱ ድርጅት በባለስልጣኑ መመዝገብ ይኖርበታል፡፡

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የተከፈለን ድርጅት ለማስመዝገብ ከሚቀረብ ማመልከቻ ጋር የሚከተሉት ሰነዶች ተያይዘው መቅረብ ይኖርባቸዋል፤

(ሀ) ድርጅቱ እንዲከፈል በድርጅቱ በመተዳደሪያ ደንቡ ወይም ሥልጣን በተሰጠው የድርጅቱ የበላይ አካል የተሰጠውን ውሳኔ፤

(ለ) ከመከፋፈሉ በፊት ድርጅቱ የነበረው የሀብትና ዕዳ መግለጫዎችና

creditors and guarantors before the organization is divided.

(6) A decision to divide the company cannot be passed without obtaining the consent of the creditors if the company that is intended to be divided is unable to fulfill its obligations.

(7) The accounts of the company to be divided should be examined from the beginning of the last accounting year until the accounts are closed and until the distribution is done.

9. <u>Registration of a divided organization</u>

(1) Every company created by division must be registered with the authority.

(2) The following documents must be submitted with an application to register a company paid in accordance with paragraph (1) of this article:

a) The resolution given by the governing body of the organization authorized by the organization to be demerged by the organization's bylaws;

b) A statement of assets and liabilities of the company prior

የንብረት ቆጠራ ዝርዝር እንዲሁም የንብረት ክፍፍሉን ዕቅድና አፈጻጸሙን የሚያሳይ መግለጫ፤

(ሐ) የድርጅቱን መብትና ግዴታ የተከፋፈለበትን ዕቅድና አፈጻጸሙን የሚያሳይ መግለጫ፤

(መ) ክፍፍሉ ከመፈጸሙ በፊት የነበረውን የድርጅቱን መተዳደሪያ ደንብ እና የምዝገባ ሰርትፍኬት፤

(ሠ) ከክፍፍሉ በፊት የነበረውን የእያንዳንዱን ድርጅት ሠራተኞች ስም ዝርዝርና የከፈሉትን የግብርና የጡረታ መዋጮ የሚያሳይ መግለጫ እንዲሁም ወደ ተከፈሉት ድርጅቶች የተላለፉትን ሠራተኞች ስም ዝርዝርና አፈጻጸሙን የሚያካትት መግለጫ፤

(ረ) ድርጅቱ ከመከፋፈሉ በፊት የተከናወነውን ወቅታዊ የኦዲት ሪፖርት፤

(ሸ) ድርጅቱ ከመከፋፈሉ በፊት በስሙ ተከፍቶ የነበረ የባንክ ሂሣብ መግለጫ፤

to the demerger and a list of assets and a statement showing the plan and implementation of the demerger of assets;

c) A statement showing the plan and implementation of the organization's rights and obligations;

d) The articles of association and certificate of registration of the company that existed before the demerger;

e) A list of the employees of each company prior to the demerger and a statement showing the agricultural pension contributions they have paid, and a statement including the names and performance of the employees transferred to the companies that have been paid;

f) The current audit report carried out before the demerger of the company;

g) Statement of bank account opened in his name before the division of the company;

h) The list of creditors before the company was liquidated and the agreement made by the creditors regarding the

(ቀ) ድርጅቱ ከመከፈሉ በፊት የነበሩ ገንዘብ ጠያቂዎች ስም ዝርዝር እና ክፍፍሉን በተመለከተ ገንዘብ ጠያቂዎች ያደረጉትን ስምምነት፤

(በ) የተከፈለውን የእያዳንዱን ድርጅት የተለያዩ የስራ አመራርና የበላይ አካል ወይም አካላት ስም፣ አድራሻ እና ዜግነት፤

(ተ) የተከፈለውን የእያንዳንዱን ድርጅት ስምና ዓርማ (ካለው)፤

(ቸ) የተከፈለው እያንዳንዱ ድርጅት የሚሰማራበትን የሥራ ዘርፍ፤

(ኀ) የተከፈለውን የእያንዳንዱን ድርጅት አድራሻ።

10. ስለመለወጥ

1) አንድ ድርጅት በመተዳደሪያ ደንቡ ላይ በተመለከተው መሠረት ወይም በድርጅቱ የበላይ አካል ውሳኔ ወደ ሌላ ዓይነት አደረጃጀት ወይም ድርጅት ሊለወጥ ይችላል።

2) በውጭ ሀገር የተመሠረተ እና በኢትዮጵያ ውስጥ ሥራ በማከናወን ያለ ድርጅት ወደ አገር በቀል ድርጅትነት ሲለወጥ የአዋጁ

liquidation;

i) The names, addresses and nationalities of the various management and governing body or bodies of each organization;

j) The name and logo (if any) of each organization demerged;

k) The field of business in which each company demerged is engaged;

l) The address of each organization demerged.

10. Conversion

(1) An organization may be transformed into another type of organization or organization based on the regulations or by the decision of the organization's governing body.

(2) When an organization based in a foreign country and doing business in Ethiopia is transformed into a local organization, the provisions of the proclamation shall apply to the

ድንጋጌዎች እንደ አግባብነቱ በሚለወጠው ድርጅት ላይ ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡

3) ለውጡ ሲፈጸም የቀድሞው ድርጅት መብትና ግዴታዎች እንዲሁም በውስጣቸው የነበሩ ሰራተኞች እንደአግባብነታቸው ወደተለወጠው ድርጅት ይተላለፋሉ፡፡

11. <u>ስለተለወጠ ድርጅት ምዝገባ</u>

1) ወደ ሌላ ዓይነት አደረጃጀት የተለወጠ ድርጅት በባለስልጣኑ እንደገና መመዝገብ ይኖርበታል፡፡

2) የተለወጠ ድርጅትን ለማስመዝገብ ከሚቀረብ ማመልከቻ ጋር የሚከተሉት ሰነዶች ተያይዘው መቅረብ ይኖርባቸዋል፤

(ሀ) ድርጅቱ ወደ ሌላ ዓይነት አደረጃጀት እንዲለወጥ በመተዳደሪያ ደንቡ ወይም ሥልጣን በተሰጠው የድርጅቱ የበላይ አካል የተሰጠውን ውሳኔ፤

(ለ) ድርጅቱ ከመለወጡ በፊት የነበረው የሀብትና ዕዳ መግለጫዎችና የንብረት ቆጠራ ዝርዝር እንዲሁም የንብረት ክፍፍሉን ዕቅድና አፈጻጸሙን የሚያሳይ መግለጫ፤

transformed organization as appropriate.

(3) When the transformation takes place, the rights and obligations of the previous organization as well as the employees in them shall be transferred to the transformed organization according to their relevance

11. Registration of transformed organization

(1) An organization that has transformed to another type of organization must be re-registered by the authority.

(2) The following documents must be submitted with the application to register a transformed company:

a) The decision given by the governing body of the organization to transform the organization into another type of organization;

b) The statement of assets and liabilities and the list of assets before the transformation of the

(ሐ) የቀድሞው ድርጅት መብትና ግዴታ ወደ ተለወጠው ድርጅት መተላለፉን የሚያሳይ መግለጫ ወይም ስምምነት፤

(መ) ድርጅቱ ከመለወጡ በፊት የነበረውን ድርጅት ሠራተኞች ስም ዝርዝርና የከፈሉትን የግብርና የጡረታ መዋጮ የሚያሳይ መግለጫ እንዲሁም ወደ ተለወጠው ድርጅት የተላለፉትን ሠራተኞች ስም ዝርዝር፤

(ሠ) ድርጅቱ ከመለወጡ በፊት የተከናወነውን ወቅታዊ የኦዲት ሪፖርት፤

(ረ) ድርጅቱ ከመለወጡ በፊት በስሙ ተከፍቶ ስለነበረው የባንክ ሂሣብ መግለጫ

(ሰ) ድርጅቱ ከመለወጡ በፊት የነበሩ ገንዘብ ጠያቂዎች ስም ዝርዝር እና

company, as well as a statement showing the plan and implementation of the distribution of assets;

c) A statement or agreement showing that the rights and obligations of the former organization have been transferred to the changed organization;

d) A list of the employees of the company before the transformation of the company and a statement showing taxes and pension contributions they have paid, as well as a list of the names of the employees who have been transferred to the transformed company;

e) A current audit report carried out prior to the change of entity;

f) Statement of the bank account opened in the company's name before the transformation;

g) The list of creditors before the change of the company and the agreement made by

የድርጅቱን መለወጥ በተመለከተ ገንዘብ ጠያቂዎች ያደረጉትን ስምምነት፤

(ሸ) የተለወጠውን ድርጅት የስራ አመራርና የበላይ አካል ወይም አካላት ስም፣ አድራሻ እና ዜግነት፤

(ቀ) የተለወጠውን ድርጅት ስምና ዓርማ (ካለው)፤

(በ) የተለወጠው ድርጅት የሚሰማራበትን የሥራ ዘርፍ፤

(ተ) የተለወጠውን ድርጅት አድራሻ፤

(ቸ) የቀድሞው ድርጅት መተዳደሪያ ደንብና እንደ አግባብነቱ የምዝገባ ምስክር ወረቀት፡፡

the creditors regarding the change of the company;

h) The name, address and nationality of the management and governing body or bodies of the changed organization;

i) The name and logo of the changed organization (if any);

j) The business field in which the converted company is engaged;

k) Address of the changed company.

l) Articles of association of the former organization and certificate of registration as applicable.

12. ስለ ደረሰኞች አጠቃቀም

1) ደረሰኝን በተመለከተ አግባብ ባለው የታክስ ሕግ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ድርጅቶች ከመዋሃዳቸው፣ አንድ ድርጅት ከመከፋፈሉ ወይም ወደ ሌላ ድርጅትነት ከመለወጡ በፊት በድርጅቶቹ ጥቅም ላይ ውለው የነበሩ ደረሰኞች ሌላ ደረሰኞች እስከሚታተሙ ድረስ ጥቅም ላይ ስለሚውልበት ሁኔታ እንደአግባብነቱ

12. Utilization of receipts

(1) Subject to the provisions of the relevant tax law regarding receipts, the receipts used by the companies before the merger of companies, the division of a company or the transformation into another

በባለስልጣኑ ሊወሰን ይችላል፡፡

2) በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ከድርጅቶች መዋሀድ፣መከፋፈል ወይም መለወጥ በኂላ አስቀድሞ ሲጠቀሙባቸው የነበሩ ደረሰኞችን ከ30 የስራ ቀናት በላይ ሊጠቀሙ አይችሉም፡፡

company may be decided by the authority as appropriate.

(2) Subject to the provisions of paragraph 1 of this article, after the merger, division or change of companies, they cannot use the invoices that they have already used for more than 30 working days.

13. <u>በመገናኛ ብዙኃን ስለማሳወቅ እና በድኅረ ገጽ ስለማውጣት</u>

1) የሚዋሃድ ወይም የሚከፈል ወይም ወደ ሌላ ድርጅት የሚለወጥ የማናቸውም ድርጅት የበላይ ኃላፊ የውህደቱ ወይም የክፍፍሉ ወይም የመለወጡ ውሳኔ በተላለፈ በ15 ቀናት ውስጥ ውሳኔውን ለአጠቃላይ ሕዝቡ ተደራሽ በሆነ ጋዜጣ ወይም መገናኛ ብዙኃን እና በድረ ገጹ ማውጣት ይኖርበታል፡፡

2) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ቢኖርም፣ የደርጅቶቹ የበላይ ኃላፊ ለታወቁ የድርጅቶቹ ለጋሾች ወይም ተጠቃሚዎች ከመገናኛ ብዙኃኑ በተጨማሪ በጽሑፍ ማሳወቅ ይችላሉ፡፡

13. <u>Informing in the media and publishing on the web</u>

(1) The chief executive of any organization that is to be merged or divided or transformed into another organization must publish the decision in a newspaper or mass media accessible to the general public within 15 days after the decision of the merger or division or change is made.

(2) Notwithstanding paragraph (1) of this article, the head of the organizations may notify the known donors or beneficiaries of the organizations in writing in addition to the media.

ክፍል ሦስት
ስለድርጅት መፍረስ

14. የድርጅቶች መፍረስ

1) በአዋጁ አንቀጽ 83 ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) በተደነገገው መሠረት አንድ ድርጅት ከሚከተሉት ምክንያቶች በአንዱ ሊፈርስ ይችላል፤

(ሀ) በመተዳደሪያ ደንቡ ሥልጣን ባለው አካል እንዲፈርስ ሲወሰን፤

(ለ) በአዋጅ አንቀጽ 70 መሠረት የሪፖርት የማቅረቢያው የጊዜ ገደብ ባለፈ በሦስት ወራት ውስጥ ሪፖርት ሳያቀርብ በመቅረቱ ሕልውናውን እንዲያረጋግጥ በጋዜጣ ጥሪ ተደርጎለት በ30 ቀናት ውስጥ ድርጅቱ ሕልውና ያለው መሆኑን ቀርቦ ባለማስረዳቱ ምክንያት የባለስልጣኑ ቦርድ እንዲፈርስ ሲወስን፤

(ሐ) በአንቀጽ 78 መሠረት አዋጁንና ሌሎች ሕጎችን በመጣሱ ምክንያት የማስተካከያ እርምጃ እዲወስድ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶት ባለማስተካከሉ ምክንያት በባለስልጣኑ ዋና ዳይሬክተር እገዳ ተጥሎበት

Part three

Dissolution of organizations

14. Dissolution of organizations

(1) According to the provisions of paragraphs 1 and 2 of Article 83 of the Proclamation, an organization may be dissolved for one of the following reasons:

a) When it is decided to be dissolved by the competent body under the by-laws;

b) When the board of the authority decides to dissolve the organization for failing to submit a report within three months after the deadline for submitting the report in accordance with article 70 of the Proclamation, and for failing to explain the existence of the organization within 30 days after being called by the newspaper to confirm its existence;

c) In accordance with Article 78, it was warned to take corrective action due to violation of the Proclamation and other laws and was suspended by the director general of the authority due to non-remedial action.

የዕገዳ ውሳኔው በተሰጠ በሦስት ወራት ውስጥ ማስተካከያ ባለማድረጉ በቦርዱ እንደፈርስ ተወስኖ ውሳኔው በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ካልተሻረ፤

(መ) በአዋጁ አንቀጽ 59 ንዑስ አንቀጽ (7) አንድ ድርጅት በማታለል ወይም በማጭበርበር የምዝገባ የምስክር ወረቀት አግኝቶ ከሆነና ይኸው በባለስልጣኑ ተረጋግጦ ቦርዱ ድርጅቱ እንዲፈርስ ሲወስን፤

(ሠ) ድርጅቱ በከባድ የወንጀል ድርጊት ወይም በተደጋጋሚ በቀላል ወንጀል በመሳተፍ ጥፋተኛ ሆኖ ከተገኘና ይኸው በፍርድ ቤት ሲወሰን፣ ወይም

(ረ) ዕዳውን የመክፈል ችሎታ የሌለው መሆኑ በፍርድ ቤት ሲወሰን፡፡

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 (ሀ) መሠረት የፈረሰ ድርጅት ውሳኔውን ለባለስልጣኑ በአሥራ አምስት ቀናት ውስጥ የማሳወቅ ግዴታ አለበት፡፡

3) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት ድርጅቱ ለባለስልጣኑ ከሚያቀርበው ማስታወቂያ ጋር ድርጅቱ እንዲፈርስ የተወሰነበትን ቃለ

d) According to Article 59 (7) of the Proclamation, if an organization has obtained a certificate of registration by deception or fraud and the same is verified by the authority and the board decides to dissolve the organization;

e) If the organization is found guilty of engaging in a serious criminal act or frequent misdemeanours and the same has been decided by a court, or

f) When it is determined by the court that it is incapable of paying its debt.

(2) Pursuant to paragraph 1(a) of this article, an organization that has been dissolved is obliged to notify the authority of its decision within fifteen days.

(3) According to paragraph 2 of this article, the company must submit the minutes of the meeting where it was decided to

ጉባኤ፣ የድርጅቱን ወቅታዊ የሥራ ክንውንና የሂሳብ ሪፖርት አያይዞ ማቅረብ አለበት።

4) የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው፣ አንድ ድርጅት ሲፈርስ የሚመራበት ሥርዓት በድርጅቱ መተዳደሪያ ደንብ ይወሰናል።

15. <u>የመፍረስ ውጤት</u>

1) እንዲፈርስ የተወሰነበት ድርጅት ንብረት በአንቀጽ 84 እና አዋጁን ለማስፈጸም በወጣው ደንብና መመሪያ መሠረት ወዲያውኑ በባለስልጣኑ በሚሾም ሒሳብ አጣሪ ኃላፊነት ሥር ሆኖ የማጣራቱ ሥራ ይከናወናል።

2) የድርጅቱ የሒሳብ ማጣራት ሥራዎች ሲጠናቀቁ፤በሒሳብ አጣሪው ጠያቂነት ባለስልጣኑ ድርጅቱን ከመዝገብ ይሰርዛል።

3) ድርጅቱ ሲፈርስ በአዋጁ አንቀጽ 84 በተደነገገው መሠረት ያለበትን ሕጋዊ ዕዳ ከፍሎ ተራፊው ንብረት

dissolve the company, the company's current operations and financial report together with the notice it submits to the authority.

(4) Subject to the provisions of this article, the procedure for the dissolution of an organization shall be determined by the organization's bylaws.

15. **<u>Effect of dissolution</u>**

(1) The property of the organization that has been decided to be dissolved shall be inspected under the responsibility of an auditor appointed by the authority in accordance with Article 84 and the regulations and directives issued to implement the proclamation.

(2) When the company's accounting operations are completed, at the request of the auditor, the authority shall cancel the company from the register.

(3) When the organization is dissolved, it shall pay its legal debt in accordance with the provisions of Article 84 of the

በድርጅቱ መተዳደሪያ ደንብ በተመለከተው መሠረት ወይም በድርጅቱ የበላይ አካል ውሳኔ ለሌላ ድርጅት የሚተላለፍ ሲሆን በመተዳደሪያ ደንቡ ወይም በድርጅቱ የበላይ አካል የተሰጠ ውሳኔ ከሌለ ባለስልጣኑ ለሌላ ድርጅት ወይም በአዋጁ መሰረት ለተቋቋመው የሲቪል ማህበረሰብ ፈንድ እንዲተላለፍ ሊወስን ይችላል፡፡

Proclamation, and the transferee's property shall be transferred to another organization in accordance with the organization's bylaws or by the decision of the governing body of the organization.

16. **ለተወሰነ ጊዜ ስለተቋቋመ በጎ አድራጎት ድርጅት**

ለተወሰነ ጊዜ የተቋቋመ የአደራ በጎ አድራጎት ድርጅት ሲፈርስ በአዋጁ አንቀጽ 45 በተደነገገው መሠረት ንብረቱን የመውሰድ መብት ያላቸው ባለገንዘቦች የአደራ በጎ አድራጎት ድርጅቱን ንብረት ማስያዝ ይችላሉ፡፡

16. **Charitable organizations established for a certain period of time**

When a charitable organization established for a certain period of time is dissolved, according to the provisions of Article 45 of the proclamation, the investors who have the right to take the property may mortgage the property of the charitable organization.

ክፍል አራት
ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

17. **የመሸጋገሪያ ድንጋጌ**

ይህ መመሪያ ከመውጣቱ በፊት የተጀመረ የመዋሃድ፣ የመከፋፈል እና የመለወጥ ሂደት፣ ቅንጅት በተጀመረበት መንገድ ይስተናገዳል፡፡

PART FOUR
MISCELLANEOUS PROVISIONS

17. **Transitional Provisions**

Any merger, division, or conversion process initiated prior to the issuance of this Directive shall be treated in the same manner as the

consolidation.

18. ***መመሪያው ስለሚሻሻልበትሁኔታ***

የባለስልጣኑ ቦርድ ይህንን መመሪያ በማናቸውም ጊዜ ሊያሻሽለው ይችላል፡፡

19. ***መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ***

ይህ መመሪያ በኢፌዲሪ የፍትህ ሚኒስቴር ከተመዘገበ በኋላ በድረገጽ ይፋ ከተደረገበት ቀን ጀምሮ ተፈፃሚነት ይኖረዋል፡፡

ጂማ ዲልቦ ደንበል
የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ባለስልጣን
ዋና ዳይሬክተር
ታህሳስ 13 ቀን 2015 ዓ.ም

18. Amendment of the directive

The Board of the authority may amend this directive at any time.

19. Effective date

This directive shall be effective from the date of its publication on the website after it has been registered with the Federal Ministry of Justice.

Jima Dilbo Denbel
Director General
Authority for civil society organizatios
22 December 2022